የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

አሥረኛ ዓመት ቁጥር ፵
አዲስ አበባ ሚያዝያ ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

10th Year No 40
ADDIS ABABA 29th April 2004


## ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፫፻፺፱/፲፱፻፺፮ ዓ.ም

ከቡርኪናፋሶ መንግሥት ጋር የተደረገ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ..... ገጽ ፪ሺ፮፻፲፰


## CONTENTS


Proclamation No. 399/2004

Government of Burkina Faso Air Transport Services Agreement Ratification Proclamation No.... Page. 2618


### አዋጅ ቁጥር ፫፻፺፱/፲፱፻፺፮ ዓ.ም

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በቡርኪናፋሶ መንግሥታት መካከል የተደረገውን የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክና በቡርኪናፋሶ መንግሥታት መካከል እ.ኤ.አ. ኦክቶበር ፲፬ ቀን ፪ሺ፫ በአዲስ አበባ ላይ የተፈረመ በመሆኑ፣

ስምምነቱ ሥራ ላይ የሚውለው ስለ ዓለም አቀፍ ስምምነት አፈጻጸም በተመለከተ ሕገ መንግሥታዊ ሥነ ሥርዓቶች መፈጸማቸውን ሁለቱ ወገኖች በዲፕሎማሲያዊ መንገድ እርስ በርሳቸው ካስታወቁበት ዕለት ጀምሮ እንደሆነ በስምምነቱ ላይ የተመለከተ በመሆኑ፣

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዝያ ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት ከሚከተለው ታውጇል::

### PROCLAMATION NO. 399/2004.

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE AIR TRANSPORT SERVICES AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF BURKINAFASO

**WHEREAS,** an Air Transport Services Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of Burkina Faso was signed in Addis Ababa, on 14th day of October, 2003;

**WHEREAS,** it is stipulated in the Agreement that the Agreement shall enter into force when both parties have notified each other through diplomatic channels the fulfillment of their constitutional formalities concerning the conclusion and implementation of international agreement;

**WHEREAS,** the House of the People's Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 29th day of April, 2004";

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub Articles (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ከቡርኪናፋሶ መንግሥት ጋር የተደረገ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፫፻፺፱/፲፱፻፺፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

## ፪. ስምምነቱ ስለመጽደቁ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በቡርኪናፋሶ መንግሥታት መካከል እ.ኤ.አ. ኦክቶበር ፲፬ ቀን ፪ሺ፫ አዲስ አበባ ላይ የተፈረመው የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ስምምነት ፀድቋል::

## ፫. የመሠረተ ልማት ሚኒስትር ሥልጣን

የመሠረተ ልማት ሚኒስትር ስምምነቱን በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል::

## ፬. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከሚያዝያ ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል::

አዲስ አበባ ሚያዝያ ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**
**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**ፕሬዚዳንት**

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Government of Burkina Faso Air Transport Services Agreement Ratification Proclamation No.399/2004."

## 2. Ratification of the Agreement

The Air Transport Services Agreement signed in Addis Ababa on the 14th day of October 2003, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of Burkina Faso, is hereby ratified.

## 3. Power of the Minister of Infrastructure

The Minister of Infrastructure is hereby empowered to undertake all acts necessary for the implementation of the Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force as of 29th day of April, 2004

**Done at Addis Ababa, this 29th day of April, 2004**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL**
**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት